# የወንጌል አገልግሎት ኅብረት
# የእምነት መግለጫ

## መግቢያ

የእምነት መግለጫ ለማንኛውም ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ወሳኝ መኾኑ አያጠያይቅም። የእምነት መግለጫ መኖሩ ብቻ ሳይኾን መጠበቁ ደግሞ ከምንም በላይ ወሳኝነት አለው። አሊያ ከእምነት መግለጫው ተቃራኒ የኾኑ የስሕተት ትምህርቶች መግባታቸውና እውነተኛውን ትምህርት መበረዛቸው አይቀርም። በልዩ ልዩ ምክንያቶች በማንነት ቀውስ ውስጥ የሚገኘው የተሐድሶ አገልግሎት አንዱ ጉድለትም፥ ይህ ነው የሚባልና ወጥ የኾነ፥ ኹሉም ማኅበራት የሚቀበሉት የእምነት መግለጫ የሌለው መኾኑ ነው። ይህን ክፍተት ለመሙላት የወንጌል አገልግሎት ማኅበራት ኅብረት ይህን የእምነት መግለጫና በዚያ ላይ የተመሠረተውን አስተምህሮና በሌሎች ከአገልግሎቱ ጋር ሊገናኙ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የያዛቸውን ዐቋሞች ያካተተውን ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጎታል።

ኅብረቱ ይህን ሰነድ፥ በዚህ ሁኔታ እንዲዘጋጅ አስፈላጊ የሆኑባቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከምክንያቶቹም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

፩. በ34 ዓ.ም በኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አማካይነት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ጵጵስና ደረጃ የተቋቋመችው በ4ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ ቢኾንም፥ ሐዋርያትን ፍሬምናጦስ የመሠረተ እምነት አስተምህሮንና ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን የተረከበው፥ ሐዋርያዊ ትውፊት ካላት ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከአቡነ አትናቴዎስ ስለ ኾነ፥ ከሐዋርያት ጀምሮ ሲያያዝ እኛ ዘንድ የደረሰው እውነተኛ ትምህርት ሳይፋለስ፥ ተቀርጾ በሰነድነት መቀመጥና መጠበቅ እንዳለበት በማመን፣ የወንጌል አገልግሎት ማኅበራት ኅብረት አባል ማኅበራት ወጥ የኾነና የጋራ የእምነት መግለጫና አስተምህሮ እንዲኖራቸው ማስፈለጉ፣

፪. አሁን ያለውም ሆነ የሚመጣው ትውልድ፥ በወንጌል አገልግሎት ዐብሮን ከመጠመዱ በፊት፥ ለአንድ ራእይ ግብ መምታት አሰባሳቢያችን በኾነው በዚህ የአስተምህሮ ማሽን ተቀርጾና ተሠርቶ ማለፍ እንዲኖርበት ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ፤

፫. በወንጌል አገልግሎት ዐብረውን የሚጠመዱ ኹሉ፥ የእኛ አስተምህሮ ከሌሎቹ በምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የእውነት መሠረት እንደሚለይ ዐውቀው እንዲያሳውቁ፤

፬. በጠላት አነሣሽነት ከተዘሩትና ከሚዘሩት እንክርዳድ ትምህርቶች ራሳችንንና የወንጌል አገልግሎታችንን ለመጠበቅ፤

፭. የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮ ለማወቅ ከሚፈልጉ ግለ ሰቦችና ቡድኖች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች፥ በአንድ አገልግሎት ያለን ኹሉ ባለን ተመሳሳይ መረዳት፥ አንድ ዐይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ መስጠት እንዲያስችለን፤

፮. ባለንበት ዘመን ክርስትናን በቅርጽ የሚመስሉ፥ በይዘት ግን ያይደሉ ዐዳዲስ ፍልስፍናዎች እየተፈጠሩ መኾኑ ሲታይ፥ መጪው ዘመን ይበልጥ አደገኛ እንደሚኾን ስለሚያመለክት፥ ትውልድንም የመጠበቅ ኀላፊነትን ለመወጣት፤

፯. የወንጌል አገልግሎት ማኅበራት ኅብረት አባል ማኅበራትም ማንነታቸውን እንዲያውቁ፥ ተገቢውን አቅጣጫ ይዘው እንዲጓዙና አገልግሎታቸውን በተገቢው መንገድ እንዲፈጽሙ ለማድረግ፣

እና በመሳሰሉት ብዙ ምክንያቶች፥ ከአበው የተላለፈው ይህ የእምነት መግለጫና አስተምህሮ በዚህ መልክ ተዘጋጅቶ በሰነድነት እንዲያዝ ተደርጓል።

# የእምነት መግለጫ

## ሀ፣ መግቢያ

ኅብረቱ ጥንታውያን የኾኑና ቅቡልነት ያላቸውን ዐምስት የእምነት መገለጫዎች፥ ማለትም፡- ጸሎተ ሃይማኖትን፥ አመክንዮ ዘሐዋርያትን፥ የገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔን፥ የኤጲፋንዮስ የእምነት መግለጫን፥ የአትናቴዎስ የሃይማኖት ውሳኔን ተቀብሎ የሚሠራባቸው ሲኾን፥ በእምነት መግለጫዎች ላይ ጥያቄ ቢነሣ፥ ወይም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተስማሚ ያልኾኑ ነጥቦች ተካተው ቢገኙ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይመዘናሉ።

### ፩፣ ጸሎተ ሃይማኖት

http://WongelAdvocate.com/pdf/NiceneCreed.pdf ይመልከቱ።

### ፪፣ አመክንዮ ዘሐዋርያት

http://WongelAdvocate.com/pdf/ApostlesCreed.pdf ይመልከቱ።

### ፫፣ የገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ

http://WongelAdvocate.com/pdf/KingGelawdewos.pdf ይመልከቱ።

### ፬፣ የኤጲፋንዮስ የሃይማኖት ውሳኔ

http://WongelAdvocate.com/pdf/EpiphaniusCreed.pdf ይመልከቱ

### ፭፣ የቅዱስ አትናቴዎስ የሃይማኖት ሥርዐት

http://WongelAdvocate.com/pdf/AthanasianCreed.pdf ይመልከቱ

### ፮፣ የቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፍ ጉባኤያት

እንደ አውሮፓውያን አቈጣጠር በ፫፻፳፭ በኒቅያ፣ በ፫፻፹፩ በቍስጥንጥንያ፣ በ፬፻፴፩ በኤፌሶን የተደረጉት ዓለም ዐቀፍ ጉባኤያትን እንቀበላለን። የወሰኑአቸውን ውሳኔያትና ያወጧቸውን የሃይማኖት መግለጫዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እየመዘንን የትምህርታችን አካል እናደርጋለን።

# ለ፤ የምናምነውና የምናስተምረው ትምህርተ ሃይማኖት

## ፩፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና

በሃይማኖተ አበው ምዕራፍ 28 ክፍል 14 ቍጥር 41፡42 እንደ ተጻፈው፥ እግዚአብሔር እውነትን የገለጸባቸው መጻሕፍት፥ ኦሪት፥ ነቢያት፥ ወንጌልና ሐዋርያት የሚባሉት ናቸው። ይህም አገላለጽ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ የሚያመለክት መኾኑ ግልጽ ነው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቍጥር ፴፱ (39) የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቍጥር ደግሞ ፳፯ (27) መጻሕፍት ሲኾኑ እነዚህን እስትንፋሰ እግዚአብሔር፥ መጻሕፍት አምላካውያት ናቸው ብለን እንቀበላለን።

### የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር

| | | |
|---|---|---|
| ፩. ኦሪት ዘፍጥረት | ፲፬. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልእ | ፳፯. ትንቢተ ዳንኤል |
| ፪. ኦሪት ዘፀአት | ፲፭. መጽሐፈ ዕዝራ | ፳፰. ትንቢተ ሆሴዕ |
| ፫. ኦሪት ዘሌዋውያን | ፲፮. መጽሐፈ ነህምያ | ፳፱. ትንቢተ አሞፅ |
| ፬. ኦሪት ዘኍልቍ | ፲፯. መጽሐፈ አስቴር | ፴. ትንቢተ ሚክያስ |
| ፭. ኦሪት ዘዳግም | ፲፰. መጽሐፈ ኢዮብ | ፴፩. ትንቢተ ኢዩኤል |
| ፮. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ | ፲፱. መዝሙረ ዳዊት | ፴፪. ትንቢተ አብድዩ |
| ፯. መጽሐፈ መሳፍንት | ፳. መጽሐፈ ምሳሌ | ፴፫. ትንቢተ ዮናስ |
| ፰. መጽሐፈ ሩት | ፳፩. መጽሐፈ መክብብ | ፴፬. ትንቢተ ናሆም |
| ፱. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ | ፳፪. ማሕልየ መሓልይ ዘሰሎሞን | ፴፭. ትንቢተ ዕንባቆም |
| ፲. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ | ፳፫. ትንቢተ ኢሳይያስ | ፴፮. ትንቢተ ሶፎንያስ |
| ፲፩. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ | ፳፬. ትንቢተ ኤርምያስ | ፴፯. ትንቢተ ሐጌ |
| ፲፪. መጽሐፈ ነገሥት ካልእ | ፳፭. ሰቈቃወ ኤርምያስ | ፴፰. ትንቢተ ዘካርያስ |
| ፲፫. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ | ፳፮. ትንቢተ ሕዝቅኤል | ፴፱. ትንቢተ ሚልክያስ |

### የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር

| | |
|---|---|
| ፩. የማቴዎስ ወንጌል | ፲፭. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ |
| ፪. የማርቆስ ወንጌል | ፲፮. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ |
| ፫. የሉቃስ ወንጌል | ፲፯. ወደ ቲቶ |
| ፬. የዮሐንስ ወንጌል | ፲፰ ወደ ፊልሞና |
| ፭. የሐዋርያት ሥራ | ፲፱. ወደ ዕብራውያን |
| ፮. ወደ ሮሜ ሰዎች | ፳. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ |
| ፯. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ | ፳፩. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ |
| ፰. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ | ፳፪. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ |
| ፱. ወደ ገላትያ ሰዎች | ፳፫. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ |
| ፲. ወደ ኤፌሶን ሰዎች | ፳፬. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ |
| ፲፩. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች | ፳፭. የያዕቆብ መልእክት |
| ፲፪. ወደ ቈላስይስ ሰዎች | ፳፮. የይሁዳ መልእክት |
| ፲፫. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ | ፳፯. የዮሐንስ ራእይ |
| ፲፬. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ | |

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱ÿ፹ ዓ.ም. በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሰፈረው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (ተጨማሪ፥ ዲዩትሮካኖኒካል Deuterocanonical መጻሕፍት) ተብለው የተጠቀሱትን መጻሕፍትም ከላይ ከተገለጹት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር እያገናዘብን እንደ

መጻሕፍት አምላካውያት ሳይኾን ለታሪክ፥ ለምክርና ለመሳሰለው ተግባር እንጠቀምባቸዋለን ወይም እንገለገልባቸዋለን። እንዲሁም በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቍጥር 19 ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳናት መጻሕፍት ዝርዝር ግርጌ የሰፈረውንና፥ "እንድትጸኑባቸው ያዘዝናቸሁ መጻሕፍት እነዚህ ናቸው። ከሐድያን ካስቀመጧቸው የሐሰት መጻሕፍት የወሰደና ንጽሕት የሆነች የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደ ሆነች አድርጎ ሕዝብን ለማሳሳት ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር ቤት ክርስቲያን ያገባ ሰው ቢኖር ይለይ።" የሚለውን ድንጋጌ እናከብራለን።

# ፪፣ አዋልድ መጻሕፍት

## ፩፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት

ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችባቸው 400 ዓመታት ውስጥ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ብሉያትንና ሐዲሳትን መሠረት አድርገው ለኑፋቄ ትምህርቶች መከላከያና ለሃይማኖት ማጽኛ የጻፏቸውን ድርሳናት፥ ተግሣጻትና ምዕዳናት፥ እንዲሁም ለቅዱሳት መጻሕፍት ማብራሪያ እንዲኾኑ የጻፏቸውን መጻሕፍተ ሊቃውንት ለነገረ መለኮት ከፍተኛ ዕገዛ እንዳላቸው በማመን በመጽሐፍ ቅዱስ እየመዘንን በአክብሮት እንገለገልባቸዋለን።

## ፪፣ ገድላት፣ ድርሳናት፣ ተኣምራትና ሌሎችም

በዚህ ስም የሚታወቁት በቅዱሳን ሰዎችና መላእክት ስም የተጻፉ ገድላት፥ ድርሳናት፥ ተኣምራት፥ መልክአ መልኮችና የመሳሰሉት መጻሕፍት ናቸው። "ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ፥ (ውጪ የሆነ) ኀይለ ቃል ያላቸውን መጻሕፍተ ታሪክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላለች አንልም። ከአሁንም ቀደም አልተቀበለችም፤ ወደፊትም አትቀበልም እንላለን።

ከወንጌል ቃል የተለየ አስተያየት፥ሥርዋጽ ያለውንና ያልተስማማውን ንባብና ልብ ወለድ ኀይለ ቃል አስፍረው የተገኙ መጻሕፍት ቢኖሩም እንኳ በበር በኩል ያልገቡ አንዳንድ ጕሕልያዎች (ቀጣፊዎች) የሰነቀሩአቸው ናቸው ብለን እንሠርዛቸዋለን እንጂ አሜን ብለን አንቀበላቸውም።"

መጽሐፍ ቅዱስን ለማብራራት ለተጻፉ አንድምታዊ ትርጓሜዎችና በሌሎች ርእሰ ጕዳዮች ላይ ለተጻፉ መጻሕፍትም ይህን መመዘኛ እንጠቀምበታለን።

# ፫፣ መሠረተ እምነት

የእምነት መግለጫዎችን መሠረት አድርገው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያዘጋጁቸውን ዐምስቱን አዕማደ ምስጢርና በእምነት መግለጫዎች ተገልጸው ሳለ፥ በአዕማደ ምስጢር ያልተካተቱትን ትምህርተ መንፈስ ቅዱስንና ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን፥ አሟልተን እናስተምራለን። ትምህርታችንም ባጭሩ የሚከተለው ነው፦

## ፩፣ ትምህርተ ሥላሴ

ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ራሱን የገለጠው በሦስት አካላት እና በዋሕድ መለኮት ነው። "እኔ እግዚአብሔር ባልሁ ጊዜ ስለ አብ፥ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ እናገራለሁ፤" በማለት ቅዱስ ባስልዮስ እንዳብራራው (ሃይ. አበው ም. ፺፯ ክ. ፩ቍ. ፮)። አንድ አምላክ እግዚአብሔር ራሱን በሚከተሉት ነገሮች በሦስትነት ገልጧል። እነርሱም አካል፥ ግብር፥ ስም ናቸው።

- የአካል ሦስትነት፡-

  አብ ፍጹም አካል አለው፤
  ወልድም ፍጹም አካል አለው፤
  መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል አለው።

- የግብር ሦስትነት፡-

  የአብ ግብሩ ወላዲነት አሥራጺነት፥
  የወልድ ግብሩ ተወላዲነት፥
  የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ሠራጺነት ነው።

ስለዚህ በግብር ስማቸው አብ ወላዲ አሥራጺ፥ ወልድ ተወላዲ፥ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላሉ።

✤ የስም ሦስትነት፡-

  አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ መባላቸው ነው።
  በሦስቱም የስምም የግብርም ተፋልሶ የለም።

✤ ኩነት (መኾን)፡-

  አብ ለራሱ ለባዊ ኾኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልብ ነው።
  ወልድ ለራሱ ነባቢ ኾኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃል ነው።
  መንፈስ ቅዱስ ለራሱ ሕያው ኾኖ ለአብና ለወልድ ሕይወት ነው፤ ይህም ምስጢር ኩነት (ከዊን) ይባላል።

✤ ነሢእ (መገናዘብ)

  አብ በወልድ ነባቢ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ነው።
  ወልድ በአብ ለባዊ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ነው።
  መንፈስ ቅዱስ በአብ ለባዊ በወልድ ነባቢ ነው፤ ይህ ምስጢር ነሢእ ይባላል።

✤ ህልውና፡-

  የሥላሴ ጽንዐተ አካላት እንደ ተጠበቀ፥ የስም፥ የግብርና የኩነት ባለቤትነት ሳይፋለስ፥ ከኩነት የተነሣ ኹለቱ አካላት በሚሠሩት ሥራ አንዱ አካል ህልው ነው (ዐብሮ ይሠራል)። እንዲሁም አንዱ አካል በሚሠራው ሥራ ሁለቱ አካላት ህልዋን ናቸው።

✤ የአንድነት ስም

  አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በወልም ሆነ በተናጠል የሚጠሩበት እግዚአብሔር፥ አምላክ፥ ፈጣሪ፥ ኤልሻዳይ፥ መለኮትና የመሳሰሉት የአንድነት ስም ይባላሉ።

  መለኮት ማለት የማይበረዝ፥ የማይለወጥ፥ የማይከፈል፥ ፍጡራን የማይጠሩበት፥ ጽኑዕ፥ ልዩ የኾነ፥ አምላካዊ ባሕርይ፥ ሥልጣን፥ ኀይል፥ ጌትነት ወይም እግዚአብሔርነት ማለት ነው።

## ፬፣ ትምህርተ ሥጋዌ

በኀጢአት የወደቀውን የሰውን ዘር ለማዳን ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋንና ነፍስን በመንሣት ተወሐደ።

### ✤ አንቀጸ ተዋሕዶ

ከተዋሕዶ በፊት ሁለት ህላዌያት የነበሩት አምላክና ሰው መባል፦

- ★ ሳይደባለቁ (ዘእንበለ ቱስሕት)
- ★ ሳይለዋወጡ (ዘእንበለ ውላጤ ወሚጠት)
- ★ አንዱ ለሌላው ባዕድ ሳይኾን (ዘእንበለ ቡዓዴ)
- ★ ሳይከፋፈሉ (ዘእንበለ ፍልጠት)

ተዓቅቦ ባለበት ተዋሕዶ አንድ ኾነዋል። ስለዚህም ጌታችን፥ አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ህላዌ የሚታወቅ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ኾኗል።

### ✤ መገናዘብን ያስከተለ ተዋሕዶ

በተዋሕዶ ምክንያት የመለኮት የኾነው ኹሉ ከመለኮት ጋር ለተወሐደው ትስብእት ገንዘቡ ኾኗል፤ የትስብእት የኾነ ኹሉ ትስብእትን ለተወሐደው መለኮት ገንዘቡ ኾኗል።

### ✤ ተዋሕዶው ዘለዓለማዊ ነው

በማሕፀነ ድንግል የተጀመረው ተዋሕዶ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ብቻ ሳይኾን፥ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ የኾነው መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በሞቱና በትንሣኤው በዕርገቱና በዳግም ምጽአቱ እስከ ዘላለምም ጸንቶ የሚኖር ተዋሕዶ ነው። በዚህም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው።

### ✤ አንቀጸ አድኅኖ

በሌላ በምንም በማንም ሊድን የማይችለውን ሰውን ለማዳን፥ ፍዳ ኀጢአት የሆነውን ሞት ይሞትለት ዘንድ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ኀጢአት ተሸክሞ ተሠቃየ፥ ታመመ፥ ተሰቀለ፥ ሞተ። በኀጢአተኛ ምትክ እንደሚሠዋው እንስሳ ምሳሌ በደሙ ኀጢአትን አስተሰረየ፤ በሞቱም የሞትን ዕዳ ከፈለ። በትንሣኤውም መጽደቃችንን አረጋገጠ። (ሮሜ 4፥24፡25)

በመኾኑም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛና በቤዛዊ ሞቱ ኀጢአተኞችን የሚያስታርቅ ሊቀ ካህናት (አስታራቂ) ነው። በእርሱ በማመን ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ፈጽሞ ያድናቸዋል። ከእርሱ በቀር ይህን ዕርቅ ሊፈጽም የሚችል ማንም የለም። ያለ እርሱ አስታራቂነት ማንም ወደ እግዚአብሔር መቅረብና የዘላለምን ሕይወት ማግኘት አይችልም።

በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በተገኘው የምሥራች ማመን ለዘላለም ሕይወት ሲያበቃ፥ አለማመን ደግሞ ለዘላለም ኵነኔ ይዳርጋል። እግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጀው የመዳን መንገድ ይኸው ብቻ እንጂ አማራጭ የለውም።

❖ በትንሣኤው ማዳኑን አበሠረ

በታላቅ ኀይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ድል መንሣቱንና ሰውን ነጻ ማውጣቱን በትንሣኤው አበሠረ።

❖ የወንጌል ብሥራት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሥልጣንን ኹሉ መያዙን ለደቀ መዛሙርቱ አበሠረና በሞቱ የሞት ዕዳቸውን እንደ ከፈለ ለሚያምኑ ኹሉ፥ በትንሣኤው የዛሬን የመንፈስ ትንሣኤና የመጪውን የሥጋ ትንሣኤ ዐረቦን (መያዣ) በስብከተ ወንጌል እንዲያስጨብጡ የምሥራች ነጋሪዎችን አሰማራ። በሐዋርያት የተጀመረው ይህ ወንጌልን የመስበክ ተልእኮ አካሉ በሆነችው በቤተ ክርስቲያን በኩል በምድር ላይ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቀጥል ነው።

## ፫፣ መንፈስ ቅዱስ

ስለ መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን መሠረት በማድረግ፥ በጸሎተ ሃይማኖት "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ" ተብሎ የተጻፈውን በመከተል፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደ ሠረጸ፥ ከወልድም እንደሚነሣ (እንደሚወስድ)፥ ከሥላሴ አንዱ አካል መሆኑን፥ በአብ ታቅዶ በወልድ የተከናወነው መዳናችንና መቀደሳችን በእርሱ እንደሚፈጸም፥ ልዩ ልዩ ሀብታትን (የጸጋ ስጦታዎችን) እንደ ወደደ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንደሚሰጥ እናምናለን።

## ፬፣ ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን አንዲት (አሐቲ)፣ ቅድስት፣ ከኹሉ በላይ በምትኾን (እንተ ላዕለ ኵሉ)፣ ሐዋርያት በሰበሰቧት (ጉባኤ ዘሐዋርያት) እንደ ኾነች እናምናለን። የክርስቶስ አካልና ኹሉን በኹሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ እንደ ኾነችም እናምናለን። ቤተ ክርስቲያን ማለት፥ ዳግም የተወለዱ የክርስቶስ ተከታዮች ኹሉ የሚገኙበት ጉባኤ (ስብስብ) ነው። ይህ ጉባኤ ቀደም ሲል የነበሩትንና ያንቀላፉትን ኹሉ፥ አሁን በዐጸደ ሥጋ ያሉትንና ወደ ፊትም የሚመጡትን ክርስቲያኖች ኹሉ ያጠቃልላል።

ቤተ ክርስቲያን አንዲትና ዓለማቀፋዊት እንደ መኾኗ መጠን በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተለያየች ብትኾንም፥ እግዚአብሔር ወዳቀደላት አንድነትና ፍጹምነት እንድትመጣ የተቻለንን እናደርጋለን። ለዚህ ዓላማ መሳካትም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትና የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መመሥረታቸውን እንደግፋለን። በአገራችን አብያተ ክርስቲያን መካከልም ለወንጌል ተልእኮ መፋጠን፥ የጋራ ችግሮችን በጋራ ለመፍታትና ሌሎች አገራዊ ጉዳዮችን በኅብረት ለማከናወን እንዲቻል ትብብር እንዲኖርና እንዲጠናከር እንሠራለን።

### ፰፡ ትንሣኤ ሙታን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት በማይገዛው አካል ተነሥቷል። በእርሱ ያመኑ ኹሉ በእምነት የተቀበሉት ዐረቦን (መያዣ) የሚገልጸውን የትንሣኤ ክብር ይቀዳጁ ዘንድ፥ የተዋረደው ሥጋቸው ተለውጦ መድኀኒታችን ከሞት የተነሣበትንና ያረገበትን፥ ዳግመኛም ተመልሶ የሚመጣበትን አካል በሚመስል አካል ይነሣሉ።አማኞች ከተነሡ በኋላ የዘላለም ሕይወት ይወርሳሉ፤ ያላመኑት ግን ወደ ዘላለም ሥቃይ ይሄዳሉ (ዳን. 12፥2)።

## ፱፡ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳት ምስጢራት መፈጸሚያ የምትገለገልባቸውን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የእግዚአብሔርን ቃል በማይቃረን ኹኔታ እንገለገልባቸዋለን።

### ፩፡ ምስጢረ ጥምቀት

- **የጥምቀት መሠረት**

ምስጢረ ጥምቀት፥ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ኹሉ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ኹሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" በሚለው በመድኀኒታችን ቃል መሠረት የሚፈጸም ነው (ማቴ. 28፥19-20)።

- **የጥምቀት ዐላማ**

የጥምቀት ዐላማ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መተባበር ነው (ሮሜ 6፥1-4)።

"ወተጠምቆትነሰ በማይ ውእቱ ተሳትፎትነ በሞተ ክርስቶስ፥ ወዕርገትነሂ እምነ ማይ ውእቱ ካዕበ አምሳለ ተንሥኦትነ ምስሌሁ። - በውሃ መጠመቃችን በክርስቶስ ሞት የመተባበራችን፥ ከውሃ ውስጥ መውጣታችን ደግሞ ከእርሱ ጋር የመነሣታችን ምሳሌ ነው" (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሣልስ፣ 1990 ገጽ 24)።

- **ጥምቀት አንዲት ናት**

ሞቱን በሚመስል ሞትና ትንሣኤውንም በሚመስል ትንሣኤ ከክርስቶስ ጋር መተባበራችንን በጥምቀት ማስታወቃችን ስለ ኾነ የክርስቶስም ኾነ የምእመን ሞትና ትንሣኤ እንደማይደገሙ ኹሉ ጥምቀትም የማትደገም አንዲት ናት።

- **የጥምቀት አፈጻጸም**

የጥምቀት አፈጻጸም በውሃ ውስጥ በማጥለቅ፥ ወይም ውሃ ቀድቶ በተጠማቂ ራስ ላይ በማፍሰስ፥ ወይም በመርጨት በቀሳውስት እጅ ይከናወናል።

ተጠማቂዎች ሕፃናት ከኾኑ በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳጊዎቻቸው ኀላፊነት፣ ዐዋቂዎች (በዕድሜ ከፍ ያሉ) ግን ካመኑና እምነታቸው ከተመረመረ በኋላ ይጠመቃሉ።

## ፪፣ ምስጢረ ቍርባን

### ❖ *መሠረቱ*

*ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስቅለቱ ዋዜማ ኅብስቱን አንሥቶ፥ (እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፤ ጽዋውንም አንሥቶ፥ እንካችሁ ጠጡ፥ ይህ ደሜ ነው፥ ይህንም ለመታሰቢያዬ አድርጉት) ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሠረት የሚፈጸም ነው።*

*የምንባርከው ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር፥ ወይኑም ከደሙ ጋር ኅብረት አለው። ከዚህ የተነሣም የክርስቶስ ሥጋና ደም ይባላል። የምእመናን አንድ አካል መኾንም ይገለጽበታል* (1ቆሮ. 10፥16-17)።

### ❖ አስፈላጊነቱ

*ምስጢረ ቍርባን የሚያስፈልገው ጌታ እስኪመጣ ድረስ የክርስቶስን ሞትና መከራ ለማሰብ፥ ትንሣኤውን ለመመስከር፥ የዳግም ምጽአቱን ተስፋ ለማስታወስ፥ ከክርስቶስ ጋርና እርስ በርሳችን ኅብረት ለማድረግ ነው።*

*በጌታ እራት መሳተፋችን እስከ ዳግም ምጽአተ ክርስቶስ ሲኾን፥ በዚያን ጊዜ በምሳሐ ደብረ ጽዮን፥ በበጉ ሰርግ እራት፥ ማለት ከጌታ ጋር በሚደረግ የእራት ግብዣ) ይጠናቀቃል።*

## ፫፣ ምስጢረ ተክሊል

*ጋብቻ አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር የሚፈጽሙት በአምላካዊ ጸጋ የሆነ ጥምረት እንደ ኾነ እናምናለን፤ በኹለቱ ሙሉ ፈቃደኛነት የሚገባበት ነው። ወንድ ለወንድ ወይም ሴት ለሴት የሚፈጸም ጋብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ የተከለከለ እና አስጸያፊ ርኵሰት ስለ ኾነ በእግዚአብሔር ቃል እንቃወማለን።*

### ❖ የድንግልና ሕይወት እና የምንኩስና ሕይወት

*ምእመናንም የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፥ የዋጃቸውን ጌታ በጋብቻ ወይም በድንግልና እንዲያገለግሉ የሚያደርጋቸው የእግዚአብሔር ጥሪ ነው። ለምሳሌ፦ ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያት ባለ ትዳሮች ነበሩ፤ ጳውሎስ ግን አላገባም። ትውፊታዊ ታሪክ እንደሚነገረውም ወንጌላዊ ዮሐንስ ድንግል ነበር።*

*ኾኖም አንዱን በጋብቻ፥ ሌላውን በድንግልና እንዲያገለግሉ የሚያደርጋቸው የእግዚአብሔር ጥሪ ነው እንጂ፥ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ባገኙትና በእግዚአብሔር ጸጋ በተሰጣቸው ሙሉ ደኅንነታቸው ላይ በተጨማሪ የሚታሰብ ነገር ለማትረፍ ብለው አይደለም። "ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፤ የምትመቸውን ረዳት እንፈጥርለት" የሚለውንና "ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለኹሉ አይቻልም።" ተብሎ በእግዚአብሔር የጸደቀውን ጋብቻ ለመተው የሚያስችል ጸጋ በድንግልና ሕይወት ያገለግሉ ዘንድ ለሚጠሩት እንደሚሰጥ እናምናለን።*

ምንኩስና፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚነግረን ከዚህ እውነት በቀር፥ የመዳን ምክንያት ሊኾን አይችልም። ከክርስትና ጋር ሊነጻጸር የማይገባው ነው። ኹሉም ምእመናን ይህን ተረድተው ምንኩስናን እንደ መጽደቂያ መንገድ እንዳያዩት ጠንክረን እናስተምራለን።

### ፬፤ ሌሎች ምስጢራት

ሌሎቹን ምስጢራት፥ ማለትም ምስጢረ ሜሮንን፥ ምስጢረ ክህነትን፥ ምስጢረ ንስሓን፥ ምስጢረ ቀንዲልን መጽሐፍ ቅዱስን በማይቃረኑበት መንገድ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊታቸውን ጠብቀን እንገለገልባቸዋለን።

## ሐ፤ ነገረ ቅዱሳን

### ፩፤ ነገረ ማርያም

በትውፊታዊ ታሪክ ትውልዷና ነገዷ የተገለጠው ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ስፍራ አላት። ስለ እርሷ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈው፥ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል የተነገራትን የምሥራች ያመነች ብፅዕት እንደ ሆነች እናስተምራለን። በሉቃስ ወንጌል 1፥47-55 እንደ ተገለጠውም ቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ በጸለየችው ጸሎት ውስጥ ያሉት ስንኞች ከተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱ መኾናቸው ሲታይ፥ ሰፊ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እንደ ነበራት ያረጋግጣል። በዚህ ጸሎትም ውስጥ፥ "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ፥ በመድኀኒቴ ሐሤት ታደርጋለች" እንዳለችው፥ በልጇ በወዳጇ ቤዛ መኾን ከዳኑት ቅዱሳን አንዷ መኾኗን እናምናለን። ስሟ ለመጨረሻ ጊዜ የተመዘገበበት ግብረ ሐዋርያት እንደሚያስረዳውም በርደተ መንፈስ ቅዱስ (በመንፈስ ቅዱስ መውረድ) ከተጐበኙት 120 ሰዎች ውስጥ አንዷ ናት (ሐ.ሥ. 1፥14-15)። ይህም የቤተ ክርስቲያን አካል መኾኗን ያስረዳል። ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ዓለምን ለማዳን፥ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ ከእርሷ እንደ ተወለደና እርሷም አምላክን በሥጋ የወለደች እንደ ኾነች እናምናለን።

### ፪፤ ቅዱሳን ሰዎች

ቅዱሳን የሚባሉት ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ፊት ቅዱሳንና ነውር የሌላቸው እንዲኾኑ በክርስቶስ የተመረጡ፥ ለእርሱ ልጆች ሊኾኑ የተወሰኑ፥ በውድ ልጁ ደም የተዋጁ፥ በኑሮአቸውም እየተቀደሱ ክርስቶስን በመምሰል የሚያድጉና የመንፈስ ፍሬ የሚታይባቸው ምእመናን ኹሉ ቅዱሳን ናቸው።

### ፫፤ ነገረ መላእክት

መላእክት ረቂቃንና ሕያዋን ፍጥረታት ሲኾኑ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ያላቸውን ከእግዚአብሔር ሲላኩ የሚያገለግሉ፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችንም ለመጠበቅ የሚመደቡ መናፍስት ናቸው (ዕብ. 1፥14)። መንፈስ እንደ ኾነው እንደ እግዚአብሔር ምሉዕ በኵለሄ ሳይኾኑ (በኹሉ ስፍራ ሳይገኙ) እግዚአብሔር በወሰነላቸው ስፍራና በመደበላቸው ሥራ ላይ ይገኛሉ። የተመደበላቸውን ሥራና ስፍራ የተዉት መላእክት ከዲያብሎስ ጋር ከክብራቸው ወድቀው አጋንንት ተብለዋል።

### ፬፣ የቅዱሳን ምልጃ

"ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤" (ያዕ. 5፥16) በተባለው መሠረት በዐጸደ ሥጋ ያሉ ቅዱሳን፥ አንዱ ስለ ሌላው እንዲጸልይና እንዲማልድ ታዟል። በዚሁ መሠረት በዐጸደ ሥጋ የሚገኝ ክርስቲያን የሌላውን ችግር በማየት፥ በመስማት ሲገነዘብ ይማልድለታል። የተቸገረውም በፊት ለፊት ንግግር፥ ወይም በሌላ ዘዴ እንዲጸለይለት ሲጠይቅ ይጸለይለታል። ለምሳሌ፦ ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ለጻፈላቸው ምእመናን ስለ ችግራቸው እንደሚጸልይላቸው ሲገልጥ፥ እነርሱም ስለ አገልግሎቱ መሳካት እንዲጸልዩለት አሳስቧል (ቈላ. 4፥ 3 -4፤ ኤፌ. 6 19)።

## መ፤ ሥርዐተ አምልኮ

አምልኮ የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ ለዋጀው ጌታ መገዛቱን የሚገልጽበት ሥርዐት እንደ መኾኑ፥ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብ ምስጋናን፥ ዝማሬን፥ ትምህርትንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። ቤተ ክርስቲያን ለሥርዐተ አምልኮ መፈጸሚያ ያዘጋጀቻቸውን ማሕሌትን፥ ሰዓታትን፥ ቅዳሴንና የመሳሰሉትን፥ እንዲሁም ንዋያተ ቅድሳትን መጽሐፍ ቅዱስን በማይቃረን ኹኔታ እንገለገልባቸዋለን።

### ❖ ጸሎት

ጸሎት ጸሎትን ወደሚሰማ እግዚአብሔር ብቻ የሚደረግ እንደ ኾነና ከእግዚአብሔር በቀር ወደማንኛውም ፍጡር መጸለይ ክርስቲያናዊ እንዳልኾነ እናምናለን።

### ❖ ጾም

ጾም ራስን ለእግዚአብሔር ለመለየትና ቅዱስ ፈቃዱን መፈጸም እንዲቻል ለተወሰነ ጊዜና ቀን የሚደረግ ሕርመተ ምግብ ወይም ሰውነትን ከምግብ መከልከል ነው። ጾም አፍኣዊ እንዳይሆን ነቢያትም ጌታችን ኢየሱስም አጥብቀው አስተምረዋል (ኢሳ.58 ፥3-7፤ ኤር. 14፥12፤ ዘካ.7፥4-10 ማቴ.6፥16-18

#### የተቀነኑ (የተወሰኑ) አጽዋማት

እስከ ዘጠኝ ሰዓትና ከዚያ በላይ ማንኛውም የምግብ ዐይነት የማይበላባቸው፥ እስከሚፈጸሙ ድረስም ከዓሣ ሥጋ በቀር የሌላ እንስሳ ሥጋና ተዋፅኦ ጭምር ፈጽሞ የማይቀመስባቸው በቤተ ክርስቲያን የተቀነኑ አጽዋማት ሰባት ናቸው። እነርሱም፦

1. በየሳምንቱ ረቡዕና ዐርብ፥ ከፋሲካ እስከ በዓለ ኀምሳ በቀር፥
2. ጾመ ነቢያት፥
3. የልደትና ጥምቀት ዋዜማዎች (ገሃድ)፥
4. ጾመ ነነዌ፥
5. ዐቢይ ጾም፥
6. ጾመ ሐዋርያት፥
7. ጾመ ፍልሰታ ለማርያም ከነሐሴ 1-16።

በዓለ ልደትና በዓለ ጥምቀት ረቡዕና ዐርብ ቢውሉ የጾም ቀን አይደሉም። የእነዚህ አጽዋማት ዐላማ ምእመናን በአንድ ልብና በአንድ ሐሳብ ተስማምተው ስለ ቤተ

ክርስቲያንና ስለ ሀገር ለመማለድ ነው። ከእነዚህ አጽዋማት አንዳንዶቹ ለምሳሌ ጾመ ፍልሰታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባለመኾኑ ታሪካዊ መሠረቱን የማንቀበለው ሲኾን፥ በሌሎቹም አጽዋማት ላይ በተለይ እንደ ዐበይት አጽዋማት በማይቈጠሩት በጾመ ነቢያት እና በጾመ ሐዋርያት ላይ ከዚህ ቀደም በቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠው አስተያየት የታሪኩ መታሰቢያ እንዳይጠፋ የመጨረሻው ሳምንት ብቻ እንዲጾም የቀረበው አስተያየት ውሳኔ እንዲያገኝና ወደ ተግባር እንዲለወጥ፥ ያለፈ ታሪክን በማስታወስ ላይ ብቻ በተመሠረቱት አጽዋማት ሳንወሰንም ከጊዜው ኹኔታ ጋር በተገናኘ በቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ጾም እየታወጀ ወደ እግዚአብሔር በንስሓ የሚቀረብበት ኹኔታ እንዲመቻች እንሠራለን (ሐዲስ ሕይወት ቊጥር 5፣ ገጽ 32-33፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻፣ 2000፣ ገጽ 37)።

## ❖ የምእመናን ግላዊ ጾም /ጾመ ፈቃድ/ የፈቃድ ጾም/

እያንዳንዱ ምእመን በግል የሚጾመውን ጾም በሚመለከት የተሰጠው መመሪያ በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 58 እና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6 በሚገባ የተገለጠ ስለ ኾነ በዚያ መመሪያ መሠረት የሚፈጸም ይኾናል። ዐላማውም፦

- ✳ ራስን በእግዚአብሔር ቃል በመመርመርና ጕድለትን በማረም ንስሓ ለመግባት።
- ✳ ውስጣዊ ማንነትን ለማስተካከልና እምነትንና መንፈሳዊ ኀይልን ለመቀበል፥ በተዋረደ መንፈስና በተሰበረ ልብ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ነው።

## ❖ ምጽዋት

ምእመናን ካላቸው ገቢ ላይ በማንሣት፥ ሠርቶ ለመኖር ዐቅም፥ ወይም ጤና፥ ወይም የሥራ ዕድል ላጡ፥ ወይም በተለያየ ምክንያት ለተቸገሩ የሰው ልጆች ርኅርኄ በማድረግ የሚቸሩት ስጦታ ምጽዋት በመባል ይታወቃል። ይህ ልግስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚፈጸም መሥዋዕትነው (ዕብ. 13፥16)።

## ❖ ዐሥራት፥ ቀዳምያት፥ በኵራት፥ ብፅዓት/ስእለት

ዐሥራት ማለት ምእመኑ ዘጠኙን ለራሱ አስቀርቶ ዐሥረኛውን እጅ ለእግዚአብሔር ወይም እርሱን ለምትወክል መንፈሳዊት ጉባኤ የሚሰጠው ነው።

በኵራት ማለት ከእንስሳት መጀመሪያ የተወለደውን ለእግዚአብሔር ወይም እርሱ ለወከላት መንፈሳዊት ጉባኤ የሚሰጥ ስጦታ ነው።

ቀዳምያት ማለት መጀመሪያ ከደረሰው እኽል ከፍሎ ለእግዚአብሔር ወይም እርሱ ለወከላት መንፈሳዊት ጉባኤ የሚሰጥ ስጦታ ነው።

ብፅዓት/ስእለት ማለት ደግሞ በራስ ፈቃድ ተነሣሥቶ ለእግዚአብሔር ለመስጠት ቃል መግባት ነው።

ከዚህም በተጨማሪ፥ ምእመን አምልኮተ እግዚአብሔር ወደሚፈጸምበት ስፍራ ሲመጣ፥ እንደ ወደደ በሙዳየ መባዕ የሚጨምረው ስጦታ መባዕ ይባላል።

በዐዲስ ኪዳን ግን የስጦታ ጕዳይ እንደ ብሉይ ኪዳን ሕግ ግዴታ የለበትም። እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ በሐዘን ወይም በግድ ሳይኾን በፍቅር እንዲሰጥ ታዟል። ኾኖም ከፍቅር

የተነሣ የሚደረግ ስጦታ በዐይነትም በመጠንም በሕግ ከታዘዘው እንደሚበልጥ ይታመናል። እኛም ዐሥራት ቀዳምያት በኵራት ብፅዓት/ ስእለት እንደ ብሉይ ኪዳን በግዴታ የሚደረግ ሳይኾን በፍቅርና በፈቃደኛነት የተመሠረተ የአምልኮት መገለጫ ስጦታ እንደ ኾነ እናምናለን፤ እናስተምራለን።

❖ በዓላት

በዓላት እግዚአብሔርን ለማሰብና ለሕዝቡ ያደረጋቸውንየማዳን ሥራዎች ለመዘከር የሚወሰኑ ልዩ ቀናትና በእነዚህም ቀናት የሚከናወኑ ሥርዐቶች ናቸው። በዚሁ መሠረት በቤተ ክርስቲያን የተደነገጉ ልዩ ልዩ በዓላት አሉ።

❖ እሑድ

ደካሞችንና ሸክም የከበደባቸውን ኹሉ ወደ እርሱ ጠርቶ ዘለዓለማዊ የኾነ መንፈሳዊ ዕረፍትን በሰጠን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ገብተናል። ይህ ዕረፍት በዕለትና በቦታ ተወስኖ የተሰጠ፥ ከተገባበት በኋላ ለድካም የሚወጣበት ሳይኾን፥ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ የሌለበት ኾኖ በሚገለጠው መንግሥተ ሰማያት ከጌታ ጋር የምንኖረው ኑሮ ነው።

ኾኖም ጌታ ከሙታን የተነሣባት፥ ከትንሣኤው ጀምሮ እስካረገበት ቀን ድረስ ደጋግሞ ራሱን ለደቀ መዛሙርቱ የገለጠባት፥ ርደተ መንፈስ ቅዱስ የተከናወነባትና የቤተ ክርስቲያን መመሥረት ይፋ የሆነባት፥ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ለሳምንታዊ ጉባኤ የተገለገሉባትና "የጌታ ቀን" ተብላ የምትታወቀው እሑድ በቤተ ክርስቲያን ደንብ ሳምንታዊ የዕረፍት ቀን ስለ ኾነች፥ ከሥጋ ድካም ለማረፍና እግዚአብሔርን በኅብረት ለማምለክ እንጠቀምባታለን።

❖ የጌታ በዓላት

በቤተ ክርስቲያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሠራቸው ታላላቅ ሥራዎች መታሰቢያ ይኾኑ ዘንድ የተሠሩትን የጌታን ዘጠኝ ዐበይትና ዘጠኝ ንኡሳት በዓላት የጌታን ሥራዎች ለማሰብና የእርሱን በጎነት ለመመስከር እንጠቀምባቸዋለን።

የዐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች ኹሉ የሕግ ፍጻሜ በኾነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስለምታምን እንደ አይሁድ ቀናትንና ወር መባቻዎችን (ሠርቀ ወርኀን) በመቍጠር እንዲሁም በዐጸደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳንንና መላእክትን በመዘከር ሥራ ፈትቶ መዋል በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ያልተመሠረተና ያልታዘዘ ከመኾኑም በላይ ድኽነትን የሚያስፋፋና የአገር እድገት ጠንቅ ነው። ስለኾነም ሰው ኹሉ የዕለት ተግባሩን በትጋት እየሠራ ከራሱ ዐልፎ ለሌሎች የሚያካፍለው ነገር እንዲኖረውና በዚህም እግዚአብሔርን እንዲያስከብር አበክረን እናስተምራለን።

# ሰ፤ ሌሎች ጕዳዮች

## ፩፥ ትውፊት

ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣውን ለክርስቲያናዊ አኗኗር፥ ለሥርዐተ አምልኮና ለመሳሰለው የሚጠቅመውን ባህል፥ ወግ፥ ሥርዐት ኹሉ የእግዚአብሔርን ቃል

እስካልተቃረነ ድረስ፥ "ትውፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢርና ትርጉም ጋር የሚቃረን አይደለም"** በሚለው መርሕ እየመረመርን እንቀበለዋለን(1ቆሮ 11፥2፤ 2ተሰ. 2፥15፤ 3፥6)።
**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓት አምልኮትና የውጪ ግንኙነት 1988 ገጽ 47

## ፲፪፣ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና አገልጋዮች

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲያያዝ መጥቶ እኛ ዘንድ በደረሰው ትውፊት መሠረት የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር ሲኖዶሳዊ ነው። በኢየሩሳሌም ለነበረው በሐዋርያት ለሚመራው ሲኖዶስ ተሳታፊና መልእክተኛ የነበረው ጳውሎስ፥ መንፈሳዊ ልጁን ቲቶን በቀርጤስ ሲሾመው፥ ቲቶም በበኩሉ በየከተማው ቀሳውስትን እንዲሾም አዘዘው። በየከተማው የተሾሙ ቀሳውስትም ዕጥፍ ድርብ ክብር (ምክዕቢተ ክብር) የተሰጣቸው ስለ ኾኑ በከተማዋቻቸው ሥር በሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት ቀሳውስትን የመሾም ሥልጣን እንደሚኖራቸው የታወቀ ነው።

በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትና በአስተዳደር ሥራ ለሚሾሙ ሰዎች የሚሰጡ የተለያዩ የማዕርግ አጠራሮችና ስሞች መጽሐፍ ቅዱስን በማይቃረንበት መንገድ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል እንላለን።

## ፲፫፣ የአብነትና የነገረ መለኮት ትምህርቶችና ትምህርት ቤቶች

የቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርቶች፣ የቤተ ክርስቲያን ሀብት የሆኑት የፊደል፣ የንባብ፣ የቊጥር፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የዘመን አቈጣጠር (ባሕረ ሐሳብ) የግእዝ ቋንቋ፣ የቅኔ ፣ የዜማና የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያን በረጅም ጊዜ ታሪኳ ያፈራቻቸው ስለ ኾኑ የመጠበቅ፣ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን የመፈጸምና የመደገፍ፣ በትምህርቶች የሚገኝ መንፈሳዊ ጸጋን የማሳደግ፣ በትምርቶቹ የሚተላለፉ የሐሰት ትምህርቶችን የመለየትና የማስወገድ፣ ትምርቶችንም ቤተ ክርስቲያንን ሊጠቅሙ በሚችሉበት ኹኔታ በማሳደግ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚደረገውን ጥረት ኹሉ የማገዝ መንፈሳዊ ኀላፊነታችንን እንወጣለን። በተጨማሪም ዘመናውያን የነገረ መለኮት ኮሌጆችንና ዩኒቨርስቲዎችን መቋቋምና መስፋፋት እንደግፋለን።

## ፲፬፣ ቅርሶችን መጠበቅ

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በረጅም ዘመን ታሪኳ ያፈራቻቸውን የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን በተመለከተ ክርስትናን፣ ራሷን ቤተ ክርስቲያንና ሀገርን ሊጠቅሙ በሚችሉበት ደረጃ እንዲጠበቁና ለክርስቲያናዊ ትምህርትና ታሪክ ማስረጃዎች በመኾናቸው ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚደረገውን ጥረት ኹሉ እናግዛለን። እነዚህን ቅርሶች የመጠበቅና የማልማት ሀገራዊና ክርስቲያናዊ ግዴታችንንም እንወጣለን።

## ፲፭፣ ሥዕላትና ቅርጻ ቅርጾች

በልዩ ልዩ መልክ የተቀረጹ ቅርጾችና ሥዕላት ያላቸውን የማስተማር ሚና እንገነዘባለን፥ ከዚህ ዐልፎ በሥዕላት በቅርጻ ቅርጾች ፊት ዕጣን ማጠን፥ ወደ ሥዕላትና ቅርጻ ቅርጾች መጸለይ፥ በሥዕላትና በቅርጻ ቅርጾች ፊት ወድቆ መስገድ በእግዚአብሔር ያልታዘዙ ተግባራት ስለ ኾኑ እንዲቀሩ እናስተምራለን።

## ፮፣ ሀገራዊ ኀላፊነትን ስለ መወጣት

ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የሰጠን መኖሪያችን ናት። ስለዚህ አገራችንን የመጠበቅ፣ የማልማት፥ መልካም ሥነ ምግባርን የማስተማር፣ የአገራችንን መልካም ባህል የመጠበቅ፥ ስለ አገራችንና መሪዎቿ የመጸለይ፥ ስለ አገር ፍቅርና ሰላም የማስተማር ኀላፊነታችንን እንወጣለን።

## ፯፣ ከመንግሥት ጋር ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነት

መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረን እስካልኾነ ድረስ መንግሥት የሚያወጣቸውን ማናቸውንም ሕጎች እንደ ዜጋ የመፈጸም ግዴታ የመኖሩን ያኽል፥ እያንዳንዱ ምእመን የሚጠበቅበትን ኹሉ ማድረግና መፈጸም ይኖርበታል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ